Changing the world
with women and girls

የፖሊሲ አጭር መግለጫ፡

# በኢትዮጵያ ሊበንና አምባሰል ወረዳዎች የሚያጋጥሙ የሴቶች የጥበቃ/ከለላ ችግሮችን ለመፍታት



# የፖሊሲ አጭር መግለጫ፡ በኢትዮጵያ ሊበንና አምባሰል ወረዳዎች የሚያጋጥሙ የሴቶች የጥበቃ/ከለላ ችግሮችን ለመፍታት

## ዓላማ

ይህ አጭር መግለጫ በሊበንና አምባሰል ወረዳዎች በተከሰተው የረዥም ጊዜ የሰብዓዊ ቀውሶች ላይ ተጨባጭ የሕይወት ተሞክሮ ባላቸው ሴት ረዳት ጥናት አድራጊዎች  የተመራ ምርምርን ያቀርባል። እነዚህ ረዳት ጥናት አድራጊዎች  እያንዳንዱን ሂደት ማለትም አጀንዳውን ከማውጣት ጀምሮ ግኝቶቹን በመቅረጽ ብሎም ምክረ-ሐሳቦችን አዘጋጅተዋል። በተጨማሪም የመግለጫውን ውጤቶች በማሰራጨትና በዚህ ውስጥ የተቀመጡትን ምክረ-ሐሳቦችን ትግበራ አፈፃፀም በመከታተል ግንባር ቀደም ናቸው። ረዳት ጥናት አድራጊዎች  የተገኙት በሴቶች በሚመሩና በአማራ ክልል አምባሰልና በኦሮሚያ ክልል ሊበን ወረዳዎች ከሚሰሩት ቤዛ እና ሴቭ ዘ ጀነሬሽን ዴቨሎፕመንት አሶሴሽን ድርጅቶች ነው።

መረጃን ለመሰብሰብ የሚያገለግሉ መሳሪያዎች አሳታፊና በእይታ ብሎም በተሞክሮአዊ ዘዴዎች ሀሳብን ለማንፀባረቅ የተዘጋጁ ነበሩ። ለምሳሌ፦ የኃይል ጉዞ መልመጃ (Power Walk)- የተዛቡ የእኩልነት እና የአካታችነትን ልዩነቶችን ቀጣይነት ባለው መንገድ በመከታተል በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉትን የተደራሽነትና የዕድል ልዩነቶችን ለማብራራት ይረዳል።

የዚህ አጭር መግለጫ ዓላማ በአምባሰልና ሊበን ወረዳዎች ሴቶች አሁን ያሉበትን ሁኔታ፣ ያቀረቧቸውን የመፍትሄ ሃሳቦችና የተጨባጭ እርምጃዎችን አስፈላጊነት በተመለከተ ለኢትዮጵያ መንግሥት አካላት፣ ለጋሾች፣ ዓለም-አቀፍ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ አገር በቀል መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችና የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ኤጀንሲዎችን -በተለይ ለብሔራዊ የጥበቃ/ከለላ ክላስተርና ስርዓተ-ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃት መከላከልና ምላሽ መስጠት ጥምረት (GBV AoR) - ለማሳወቅ ነው። በሁለቱ ክልሎች በተከሰተውና  ትኩርት ባልተሰጠው ቀውስ ምክንያት የተሻሉ የሴቶች ጥበቃ አገልግሎቶችን ለማሻሻል የሚያስችሉ ተጨባጭ የህይወት ተሞክሮዎችን፣ የስርዓት ክፍተቶችንና ሊተገበሩ የሚችሉ ምክረ-ሐሳቦችን ይዘረዝራል።

## ማጠቃለያ

በጥናቱ ውጤት መሰረት በሊበንና አምባሰል ወረዳዎች የሚገኙ ሴቶች ከጥበቃ/ከለላ፣ ክብርና ደህንነት ጋር የተያያዙ ውስብስብና ተደራራቢ ችግሮች ገጥመዋቸዋል። የእነዚህ ችግሮች ዋነኛ መሰረት የጾጥታ ችግር ፤ የማህበራዊ መገለል፣ የአካባቢ መራቆትና ስር የሰደደ የተዛባ የስርዓተ-ጾታ ግንኙነት ሲሆን እነዚህም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተከሰቱት ግጭቶችና በድርቅ ምክንያት የበለጠ ተባብሰዋል። በሊበን ወረዳ የረዥም ጊዜ ድርቅ፣ የደን መጨፍጨፍና የአየር ንብረት ለውጥ የሴቶች የዕለት ተዕለት ተግባራት ላይ ጫና በመጨመር ለስርዓተ-ጾታን መሰረት ላደረጉ ጥቃቶች (GBV) ተጋላጭነትን እንዴት እያባባሰ እንደሆነ ረዳት ጥናት አድራጊዎች ዘግበዋል። በተጨማሪም ጥናቱ በሁለቱም አካባቢዎች የተፈጠሩት የጾጥታ ችግርና ግጭቶች ባህላዊ የድጋፍ ስርዓቶችንና የህግ ማስከበር ሰራዎችን በማዳከሙ የሴቶች ፍትህና ጥበቃን የማግኘት እድል ውስን መሆኑን አሳይቷል። በአካባቢዎች ባሉት ችግሮችና ጥቃቶች ምክንያት የተፈጠሩት መፈናቀሎች ሴቶችን የበለጠ ተጋላጭ ያደረገ ሲሆን ይህም ኢኮኖሚያዊ ነጻነታቸውንና የማህበረሰብ ግንኙነታቸውን ያናጋዋል።

እነዚህ ችግሮች ቢኖሩም ሴቶች ግን መደበኛ ባልሆኑ የድጋፍ ትስስሮች አማካኝነት በኢኮኖሚ ተግባራትና የሰላም ግንባታ ጥረቶች ላይ አስደናቂ ጽናትን እንዳሳዩ የጥናቱ ውጤት ያሳያል። የሴቶችን የጥበቃ ችግሮች ዋና መንስኤዎችን በዘላቂነት ለመፍታት ሁሉን-ዓቀፍ፣ ስርዓተ-ጾታን መሰረት ያደረገ- ሴቶችን ግንባር ቀደምና ማዕከል ያደረገ ዘዴ- እና የተዛባ መዋቅራዊ ችግሮች ላይ ያነጣጠረ ማሻሻያ በአስቸኳይ ያስፈልጋል።

በመሆኑም ይህ የፖሊሲ ሪፖርት ወደ ቁልፍ ምክረ-ሐሳቦች ከመግባቱ በፊት በሁለቱም ወረዳዎች ያሉ የሴቶች ጥበቃ ጉዳዮች ዋና መንሰኤዎችን ብሎም ሴቶች ችግሮችን ለመፍታት የተጠቀሙባቸውን ስልቶች ይዘረዝራል።

## ከሴቶች ጥበቃ/ከለላ ጋር የተያያዙ ችግሮች ዋነኛ መንስኤዎች

በሊበንና አምባሰል ወረዳዎች የሴቶች ጥበቃ ችግሮች ዋነኛ መንስኤዎች የአየር ንብረት ለውጥ፣ መፈናቀልና ግጭቶች ናቸው። እነዚህ ተደራራቢ የተጋላጭነት መንስኤዎች የሴቶችን ደህንነት፣ ራስን በራስ የማስተዳደርና አስፈላጊ አገልግሎቶችን የማግኘት ዕድልን ያሳጣሉ። የሚቀጥለው ክፍል በቀጥታ ከረዳት ጥናት አድራጊዎች  የጥናት ግኝቶችና ሀሳቦች በመነሳት እነዚህን ጉዳዮች በዝርዝር ያብራራል።

በሊበን ወረዳ አካባቢያዊ ጫናዎች የሴቶች ተጋላጭነት ዋነኛ መንስኤዎች ናቸው። በአየር ንብረት ለውጥ፣ደን መጨፍጨፍና የተፈጥሮ ሐብት መመናመን ምክንያት የረዥም ጊዜ ድርቅ በመከሰቱ ሴቶች ረጅም ርቀት በመጓዝ ውሃ እንዲቀዱና ምግብ እንዲያመጡ ይገደዳሉ፣ ይሄም ለጥቃት ያላቸውን ተጋላጭነት ይጨምራል። ይሄንን በተመለከተ አንድ ሴት እንደገለጸችው “ድርቁ ውኃ ለማምጣት ረጅም ርቀት እንድንጓዝ ስለሚያስገድደን ለስራም ሆነ ለትምህርት የምናሳልፈው ጊዜ እንዲቀንስና ለጥቃት እንድንጋለጥ አድርጎናል።” እነዚህ አካባቢያዊ ችግሮች ቀደም ሲል ዝቅተኛ የኢኮኖሚ ደረጃ በሌላቸው ቤተሰቦች ላይም ቢሆን ኑሮአቸውን አናግቷል።

በተመሳሳይም ግጭቶችና የጸጥታ ችግር ባህላዊና ማህበራዊ ግንኙነቶችን ብሎም የአስተዳደር መዋቅሮችን አፈራርሷል። ይህም ሴቶች ጉዳት በሚደርስባቸው ጊዜ የህግ ከለላና እርዳታ እንዳያገኙ አድርጓቸዋል። የዚህ ሪፖርት አንድ ረዳት ተመራማሪ “በጦርነት ጊዜ ሁሉንም ነገር ማለትም ቤታችንን፣ ቤተሰባችንንና ደህንነታችንን እናጣለን” ስትል የደረሰውን ውድመት ገልጻለች።  ሌላ ሴት ደግሞ“እዚህ ምንም ደህንነት የለም፣ ስራም የለም ስለሆነም ለልጆቼ የምሰጠው ምንም ነገር የለኝም” ስትል ተናግራለች።

በተጨማሪም በአየር ንብረትም ሆነ በግጭት ወይም በሁለቱም ምክንያት መፈናቀል ከባድ የሆነ ተጽዕኖ አለው። ከአካባቢያቸው የተፈናቀሉ ሴቶች ኢኮኖሚያዊ ነፃነትና ማህበራዊ የድጋፍ ስርዓቶችን ያጣሉ ብሎም ለጥቃትና መገለል የበለጠ ተጋላጭ እንደሚያደርጋቸው

“ድርቁ ውኃ ለማምጣት ረጅም ርቀት እንድንጓዝ ስለሚያስገድደን ለስራም ሆነ ለትምህርት የምናሳልፈው ጊዜ እንዲቀንስና ለጥቃት እንድንጋለጥ አድርጎናል።”

ጥናቱ ያሳያል። ተደራራቢ ተጋላጭነት ያለባቸው ሴቶች እንደ አረጋውያን፣ የአካል ጉዳት ያለባቸው ወይም አናሳ የብሔር ወይም የኃይማኖት አባላት ያሉት ተደራራቢ ችግር ያጋጥማቸዋል። “እንደ የተሻለ የውሃ አቅርቦት፣ ደህንነቱ የተጠበቁ ምቹ ቦታዎችና ሰላማዊ ህይወት ያሉ የረዥም ጊዜ መፍትሄዎች እንፈልጋለን” ሲትል አንዲት ረዳት ተመራማሪ አሳሰባለች።

በአምባሰል ወረዳ የተከሰተው ግጭት የማህበራዊና የህግ ጥበቃ ስርዓቶችን በሙሉ በማፈራረስ ሴቶችን ለዘለቄታዊ የጥቃት ስጋት ሲዳርግ አጥፊዎችን ደግሞ እንዳይቀጡ እንዳደረገ በጥናቱ ተገልጿል። የ36 ዓመቷ ረዳት ተመራማሪ በሶስት ወር ውስጥ ከእስር በተለቀቀው ባለቤቷ ከቤቷ በኃይል ከተፈናቀለች በኋላ “ስርቼ ቤተሰቤን ማስተዳደር እንድችል ፍትህ ባገኝና ስራ ባገኝ ምኞቴ ነው” ብላለች። የሕግ ስርዓቶች ብዙውን ጊዜ ተደራሽ አይደሉም ብሎም ወገንተኛ ናቸው፤ ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች በበቀል ፍርሃት ምክንያት የደረሰባቸውን እንዳይናገሩ ተስፋ ያስቆርጣቸዋል።

በአምባሰል ወረዳ ያሉ ሴቶችና ልጃገረዶች ስር በሰደደ የደህንነት እጦትና ጥቃት በመጋለጣቸው ምክንያት የአዕምሮ ጤናና የስነ ልቦናና-ማህበራዊ ችግር ተንሰራፍቷል። ይሁን እንጅ የድጋፍ አገልግሎቶች በአብዛኛው አይገኙም፣ እንዲሁም መገለል ብዙዎች እርዳታ እንዳያገኙ አድርጓቸዋል። የኢኮኖሚ አለመረጋጋት የበለጠ ተጋላጭነትን ያባብሳል። አንዲት ረዳት ተመራማሪ እንደገለጸችው “በኢኮኖሚ ቀውስ ውስጥ ነን፤ በፀጥታ ችግር ምክንያት ሕይወት አስቸጋሪ ሆኗል። በምናገኘው ትንሽ ገንዘብ ከአሁን በኋላ ስራ መስራት አንችልም።” በግጭት ምክንያት የተፈጠረው የሀብት እጥረት የምግብ፣ የጤና እንክብካቤና የገቢ ማስገኛ ዕድሎችን አጥፍቷል።

የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳየው በግጭቶችና በድርቅ ወቅት ያለው የሀብት እጥረት የጤና አጠባበቅ አቅርቦትን በእጅጉ ስለሚገድብ ሴቶችና ህጻናት በህክምና አገልግሎት እጥረት እንዲሰቃዩ አድርጓል። ይህም መከላከል ወደማንችላቸው የጤና ችግሮች ያመራና ለእናቶችና ህጻናት ሞት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል። ነፍሰ ጡር እናቶች በጣም ተጋላጭ ከሆኑ ቡድኖች መካከል ናቸው፤ በተለይም ርቀት ባለባቸው ወይም ግጭት በተከሰተባቸው አካባቢዎች የሚኖሩት በቂ የጤና አገልግሎት ለማግኘት ትልቅ ተግዳሮቶች ያጋጥማቸዋል።

የሴቶች የተለያዩ ተደራራቢ ሁኔታዎች ማለትም እንደ እድሜ፣ የአካል ጉዳት፣ የጋብቻ ሁኔታና መፈናቀል መገለላቸውን የበለጠ ያጠናክራል። ለምሳሌ፦ “አረጋውያን ሴቶች ወይም የአካል ጉዳት ያለባቸው ሴቶች በድርቅ ጊዜ ወይም በሚፈናቀሉበት ወቅት ከእንቅስቃሴ ጋር ተያይዞ በሚገጥም ችግር ምክንያት በድጋፍ እጥረት የበለጠ ይሰቃያሉ” ሲሉ አንዲት ረዳት ተመራማሪ አብራርታለች። እነዚህ ውስብስብ ችግሮች እንደ ጤና፣ ትምህርት፣ ፍትህና ጥበቃ ያሉ መሰረታዊ አገልግሎቶችን ተደራሽነት ይገድባሉ።

እነዚህ ሁኔታዎች ሁሉ አንድ ላይ በመሆን ትኩረት ባልተሰጣችው ቀውሶች ውስጥ የሴቶች ጥበቃ ጉዳዮች ከአንድ ምክንያት እንዳልመጡ ያሳያሉ፤ ነገር ግን ከአካባቢያዊ ውድቀት፣ ጥቃት፣ ግጭት፣ የተበላሹ የፍትህ ሥርዓቶች፣ ስርዓተ-ጾታን መሰረት ካደረጉ መድሎዎችና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ጥምረት የመነጩ መሆናቸውን ያሳያሉ። በሁለቱም ወረዳዎች የሚገኙ ሴት አመራሮች የውሃና የመሬት አቅርቦትን ወደ ነበሩበት መመለስ፣ የህግ ጥበቃን ማሻሻል፣ የአዕምሮ ጤና አገልግሎትን ማስፋፋት፣ ኢኮኖሚያዊ አቅምን ማጎልበትና የተገለሉ ሴቶች በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ ቀጥተኛ ተሳታፊ እንዲሆኑ የሚያካትቱ ዘላቂ ስርዓተ-ጾታ ተኮር እርምጃዎችን ጠይቀዋል።

## ሴቶች የገጠሟቸውን ችግሮችን ለመፍታት የተጠቀሙባቸው ስልቶች

በነዚህ  አካባቢዎች ያሉ ሴቶች ከፍተኛ ችግሮች ቢገጥሟቸውም የተለያዩ የችግር አፈታት ዘዴዎችን በመጠቀም ጽናትንና ውሳኔ ሰጭነትን እንዳሳዩ የጥናቱ ውጤት ያመለክታል። በርካታ ሴቶች መደበኛ ያልሆኑ የድጋፍ ሰንሰለቶችንና ማህበራትን ይመሰርታሉ፣ ኃብትን በመጋራት ይጠቀማሉ ብሎም እንዳቸው ለሌላኛው ስሜት ድጋፍ ይሰጣሉ። ጥቃቅን የንግድ ስራዎች፣ ዘላቂነት ያለው የእርሻና የእንስሳት እርባታ በተወሰነ ደረጃ የኢኮኖሚ ነፃነትን ለማስጠበቅ የሚረዱ በአካባቢው የሚገኙ የገቢ ማስገኛ ተግባራት ናቸው።

የስነ-ልቦናና ማህበራዊ ችግሮችን መፍታትም ወሳኝ ነው። ምንም እንኳን መገለልና የተዛባ የስርዓት እኩልነት ብዙውን ጊዜ መደበኛ አገልግሎቶችን ለማግኘት የሚጎዳ ቢሆንም ሴቶች ከባህላዊ ልምምዶች፣ መንፈሳዊ እምነቶችና ከመንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ከሚሰጡት ውስን ድጋፎች ጥንካሬን ያገኛሉ። ምንም እንኳን አስጊና አደገኛ ነገሮች ቢኖሩም በርካታ ሴቶች በሰላም ግንባታና በማህበረሰብ ውይይቶች ላይ በንቃት ይሳተፋሉ፣ የአሰራር  ለውጥንም እንዲኖር ይሟገታሉ። ይሁን እንጂ ውጤታማ ተቋማዊ ምላሽ አለመኖር፤ መገለል እና የበቀል ፍርሃት በርካታ ጾታዊ ጥቃት የደረሰባቸውን ሴቶች  ዝም ማሰኘቱን ቀጥሏል።

## ለተደራራቢ ሁኔታዎች ተጋላጭ የሆኑ ሴቶች ጥበቃ/ከለላ ማረጋገጥን በተመለከተ የሴቶች እይታ

የኃይል ጉዞ መልመጃ   (Power Walk) ሴቶች የዕለት ተዕለት ሁኔታቸውን በሚቀርጹ እንደ ጾታ፣ ድህነት፣ አካል ጉዳተኝነትና ስርዓታዊ መገለል ባሉ ተደራራቢ ሁኔታዎች አለመመጣጠን ላይ በጥልቀት እንዲያንፀባርቁ ቦታ ይሰጣቸዋል። ረዳት ጥናት አድራጊዎች  የተለያዩ ሚናዎችን በማካተት የሰውን ችግር እንደራስ ማየት

ችለዋል ብሎም የተዛባ የኃይል ግንኙነት በመሰረታዊ መብቶችና አገልግሎቶች ተደራሽነት ላይ እንዴት ተጽዕኖ እንደሚያሳድር ያላቸውን ግንዛቤ አሳድጓል። በርካታ ሴቶች በሰርዓቶችና በአካባቢያቸው ባሉ መሪዎች መረሳታቸውን ገልጸዋል፤ አንደኛዋ ሴት “ለቤተሰቤ ምግብና ውኃ ማቅረብ በማልችልበት ጊዜ አቅመ ቢስነት ይሰማኛል” ብላለች። ሌሎች ደግሞ ስርዓተ-ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች፣ የውሳኔ ሰጪነት አቅም ማነስና መዋቅራዊ ቸልተኝነት የሚያስከትሉትን ተያያዥ ተጽእኖዎች አንስተዋል።

ክዚህ ባሻገር መልመጃው የጥንካሬ ምንጮችም መነሻ ሁኗል። ሴቶች በህብረትና የጋራ እርምጃ በመውሰድ አቅም አግኝተዋል - “ችግሮችን ለመፍታት ከሌሎች ሴቶች ጋር ስገናኝ አቅም እንዳገኘሁ ይሰማኛል” ሲሉ አንዲት ረዳት ተመራማሪ ተናግራለች። ተንቀሳቃሽ ክሊኒኮች፣ ተደራሽ ትምህርት ቤቶችና ችግር የደረሰባቸውን ሰዎች መሰረት ያደረገ ሰብዓዊ ዕርዳታን ጨምሮ በጣም ተጋላጭ ለሆኑ ሰዎች የተዘጋጀ አገልግሎት እንደሚያስፈልግ አስምረውበታል። የማህበረሰብ ተኮር ትስስሮች ሀብቶችን ለመጋራት፣ ስለ አካታችነት ለመሟገትና የስሜት ጥንካሬን ለመገንባት አስፈላጊ ተደርገው ይታዩ ነበር።

ዘላቂ ለውጥ ሁሉን-ዓቀፍ አገልግሎቶችን ብቻ ሳይሆን የኃይል ሚዛንን መረዳትና የመፍትሄ አቅጣጫዎችን መቀየር እንደሚያስፈልግ ሴት መሪዎች አሳስበዋል። አንዲት ሴት እንዳመለከተችው፣ “የኃይልን ሚዛንን ችላ ካልን ምንም ለውጥ ማምጣት አይቻልም። ሴቶች ድሃ፣ ያልተማሩና ደህንነታቸው ያልተጠበቁ ሁነው ይቀራሉ።” ትምህርት፣ የክህሎት ስልጠናና ከጥቃትና መድልዎ ነጻ የሆኑ ምቹ ቦታዎች ለውሳኔ ሰጭነት ግንባታ ወሳኝ እንደሆኑ ተለይቷል። የተገለሉ ሴቶችን በፖሊሲና በፕሮግራም ቀረጻ ጊዜ ማዳመጥ ብሎም ትርጉም ባለው መልኩ ማሳተፍ ለረጅም ጊዜ ወደ ኋላ ያስቀሯቸውን ስርዓቶችን ለመለወጥ ቁልፍ ነገር ነው።

## ማጠቃለያ

የአየር ንብረት አደጋዎች ያመጣቸው የተወሳሰቡ ቀውሶች፣ ግጭት፣ መፈናቀልና ማህበራዊ መገለል የሴቶችን ለጥቃት፣ ለድህነትና ለመገለል ያላቸውን ተጋላጭነት አባብሰዋል። ነገር ግን በተራዘሙና ትኩረት ባልተሰጣቸው ቀውሶች ያሉባቸው አካባቢዎች ያሉ ሴቶች ዝም ብለው ተጎጂዎች ሳይሆኑ ንቁ የለውጥ አራማጆች፣ ተሟጋቾችና በማህበረሰባቸው ውስጥ መሪዎች ናቸው። ለውጤታማና ዘላቂነት ላለው ለውጥ ፖሊሲዎችና መርሃ ግብሮች ከአጭር ጊዜ የእፎይታ ስራ በመውጣት የእኩልነት መዋቅራዊ መንስኤዎችን ለመፍታት፣ ለሴቶች ደህንነትና ማብቃት ቅድሚያ በመስጠትና በሰብዓዊ ተግባራትና የሰላም ግንባታ ጥረቶች ላይ መሪነታቸውን ማዕከል እንዲያደርጉ ይጠይቃል። ማህበረሰቡ ፍትህን፣ ሰላምንና ፍትሃዊነትን ማስፈን የሚችለው ቀጣይነት ባለው የተቀናጀ ተግባር ሴቶችን በማዳመጥና ትኩረት በማድረግ ብቻ ነው።

## የድርጊት ጥሪ

ችላ የተባሉ ቀውሶች የተቀናጁ፣ ለሰርዓተ-ጾታ ምላሽ የሚሰጡ ስልቶችን ይፈልጋሉ። በተደራራቢና የተራዘሙ ቀውሶች ላይ ተጨባጭ የህይወት ተሞክሮ ያላቸው ሴቶች- በአብዛኛው በስልጣን ላይ ባሉ አካላት ትኩረት ስለማይሰጣቸው በቂ የገንዘብ ድጋፍ አያገኙም - ስለዚህ ምላሹን መምራት እንዲችሉ የእነሱ ሀሳቦች የፕሮግራሞችን ዝግጅትና ትግበራ መቅረጽ አለበት።
የመንግስት አካላት፣ ለጋሾች፣ ዓለም-አቀፍና አገር በቀል መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የሲቪል ማህበረሰብና የተባበሩት መንግስታት አጋሮች ምክረ-ሀሳቦችን የሚደግፉ ሀብቶችንና ፖሊሲዎችን ማቀናጀት፣ ብሎም ከጥቃት፣ ከድህነትና መገለል ነጻ የሆኑ ማህበረሰቦችን መገንባት አለባቸው።
ሁሉም ባለድርሻ አካላት በአገር በቀል የሚመሩ ፕሮግራሞችን ለመደገፍ—ለሴቶች አመራር እውቅና በመስጠትና በመደገፍ፣ ድምፃቸውን በማክበርና በውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች ላይ ትርጉም ያለው ተሳትፎን በማረጋገጥ ዘላቂና ሁሉን አቀፍ መፍትሄዎችን ለማጎልበት ቁርጠኛ እንዲሆኑ እናሳስባለን።

# የፖሊሲ ምክረ-ሐሳቦች

## ለሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ለዓለም-አቀፍ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ለአገር በቀል መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች

• ጎጂ የሆኑ የሰርዓተ-ጾታ ልማዶችን ለመከላከል ማህበረሰቡን ያሳትፉ ወንዶችና ወንድ ልጆችን ጥቃትን ለመከላከል አጋሮች በማድረግ የግንዛቤ ማስጨበጫ ዘመቻዎች  ማካሄድ

• በአካባቢ አስተዳደር፣ በሰብዓዊ አገልግሎት ምላሽ እቅድ ዝግጅት፣ በማህበረሰብ ውሳኔ አሰጣጥ ፤ በሰላም ግንባታ ሂደቶች ላይ ለሴቶች ትርጉም ያለው ተሳትፎ ደህንነቱ የተጠበቀና አካታች ምቹ ቦታዎችን ይፍጠሩ

• አገልግሎቶች ለተገለሉ ቡድኖች መድረሳቸውን ያረጋግጡ - የተፈናቀሉ ሴቶችን፣ አፍላ ወጣት ልጃገረዶችንና የአካል ጉዳት ያለባቸውን ሴቶችን ጨምሮ - ለማህበረሰብ ሠራተኞች የአዕምሮ ጠባሳን የሚያክም/መሰረት ያደረገ/ ስልጠና  ላይ ኢንቨስት በማድረግና ለሰርዓተ-ጾታ ትኩረት የሚሰጡ ዘዴዎችን ወደ ጥበቃና ግጭት መከላከል  ስልቶች ማካተት

• በራስ መተማመንን፣ ውሳኔ ሰጭነትንና መሪነትን ለማሳደግ ከሴቶች ፍላጎት ጋር የተጣጣመ የረጅም ጊዜ የትምህርትና የክህሎት ግንባታ ፕሮግራሞችን መደገፍ

• ለኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች የማይበገሩ ሴቶች መር የሆኑ የገቢ ማስገኛ ተግባራትን፣ የማይክሮ ፋይናንስ ተደራሽነትና የማህበራት ሞዴሎችን ፕሮግራሞች ላይ ኢንቨስት ያድርጉ

## ለፍትህ ሚኒስቴር

• የህግና የፍትህ ስርዓቶችን በማጠናከር ጥቃት ፈጻሚዎችን ተጠያቂ ለማድረግና ጉዳት ለደረሰባቸው ተደራሽና ክብር ያለው እርዳታ ለመስጠት፤ ተደራሽነትንና መተማመንን ለማሻሻል ማህበረሰቡን መሰረት ያደረጉ የፍትህ ስራዎችን መደገፍ።

## ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር

• የጤና እንክብካቤና የስነ-ልቦናና ማህበራዊ ድጋፍ ተደራሽነትን በማስፋት ተንቀሳቃሽ የጤና ቡድኖች፣ የተሻሻለ የትራንስፖርት አገልግሎትና አካል ጉዳተኝነትን ያካተተ መሰረተ ልማት መገንባት።

## ለሁሉም ባለድርሻ አካላት

• የሴቶችንና ልጃገረዶችን ጥበቃ/ከለላ ለማረጋገጥ ቀውሶች ባሉበት ጊዜ ሰብዓዊ ምላሾች በሚሰጡበት ወቅት ትርጉም ያለው የሴቶች ተሳትፎና ውሳኔን ሰጭነትን ማሳደግ።

# ምስጋና

ይህ የፖሊሲ አጭር መግለጫ የተዘጋጀው በማርቲና ሌቺ (ከአክሽን ኤይድ ዩናይትድ ኪንግደም) ሲሆን አስፈላጊ ግብዓትና ግምገማ ደግሞ በመስረት አምሳሉ፣ ሰላማዊት አድነው፣ መቅደላዊት ግርማና ንጉስ ሰማኔ (ከአክሽን ኤይድ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ)፣ ፍቅርተ ዘውዱ (ከኢትዮጵያ ሴቶችና ሕጻናት ማህበራት ህብረት)፣ ሃኒያ ሙህመድ፣ ሰምሃር ሙህመድና ሐረገወይን አሰማማው (ከቤዛ ለሴቶች የማህበረሰብ አቀፍ ልማት ማህበር) እና ራሄል ንጋቱ፣ አይናለም ጌታቸው፣ ፎዚያ ሙህመድና እየሩሳሌም ዳንኤል (ከሴብ ዘ ጀነሬሽን ዲቨሎፕመንት ማህበር) አማካኝነት ተካሂዷል።

ለዚህ መግለጫ መነሻ የሆነው ጥናት በቤዛ ለሴቶች ማህበረሰብ አቀፍ ልማት ማህበር (ቤዛ)፣ ሴብ ዘ ጀነሬሽን ዴቨሎፕመንት አሶሴሽን፣ የኢትዮጵያ ሴቶች እና ሕጻናት ማህበር ከአክሽን ኤይድ ኢትዮጵያ ጋር በመተባበር የተካሄደ ነው።

ይህን የጥናትና የፖሊሲ አጭር መግለጫ ለማዘጋጀት፣ ለመተርጎምና ዲዛይን ለማድረግ የገንዘብ ድጋፍ ላደረጉ ፒፕል ፖስት ኮድ ሎተሪ ተጫዋቾች እናመሰግናለን።

ድህረ ገጽ:
https://ethiopia.actionaid.org

ኢሜይል:
comms.ethiopia@actionaid.org ወይም
admin.ethiopia@actionaid.org

ስልክ:
+251-932-025-053 እና +251-932-024-633

ትዊተር/ኤክስ:
https://x.com/ActionaidE

ሊንክዲን:
https://www.linkedin.com/groups/13190960/

ፌስቡክ:
https://www.facebook.com/actionaidethiopia

አድራሻ:
ለሚ ኩራ፣ ወረዳ 13፣ የቤት ቁጥር 3044 (ከሲኤምሲ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ጀርባ)
https://maps.app.goo.gl/uNJ5NLdSpWbcQ63R6

ፖስታ ሳጥን ቁጥር: 1261, አዲስ አበባ, ኢትዮጵያ

የነጻ የስልክ መሰመር: 8193

# ማጣቀሻ

1 ረዳት ጥናት አድራጊዎች፡ በፌሚኒስት አሳታፊ ድርጊታዊ ምርምር (FPAR) ከተሳታፊ ይልቅ ረዳት ጥናት አድራጊዎች፡ የሚለውን ቃል እንጠቀማለን። ይህ ቃል በጥናቱ ውስጥ የተሳተፉትን በሙሉ እንደ እውቀት ባለቤቶች እኩል ጠቀሜታ እንዳላቸው ይገነዘባል። የፌሚኒስት አሳታፊ ድርጊታዊ ምርምር ከኤክስትራክቲቭ ምርምር ለመውጣት ይፈልጋል ስለዚህም ረዳት ጥናት አድራጊዎች፡ ትንታኔዎችንና ግኝቶችን በመስራት ያረጋግጣሉ።

2 የኃይል ጉዞ በአክሽን ኤይድ የፌሚኒስት ምርምር ውስጥ የስርዓተ-ጾታና ሌሎች ከማንነት ጋር የተያያዙ ምክንያቶች የመብቶች፣ የሃብቶችና የጥበቃ ተደራሽነት እኩልነትን እንዴት እንደሚቀርጹ ለማሳየት ጥቅም ላይ የሚውል አሳታፊ መሳሪያ ነው። ተሳታፊዎች የተለያዩ ማህበራዊ ሚናዎችን ይወስዱና በሁኔታዎች ላይ ለተመሰረቱ ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ፣ ይህም የተገለሉ ቡድኖች የሚያጋጥሟቸውን የተዛባ የኃይል ግንኙነትና የስርዓት ችግሮች እንዲታዩ ያደርጋሉ።

ActionAid UK

33-39 Bowling
Green Lane
London EC1R 0BJ

www.actionaid.org.uk

@ActionAidUK
ActionAidUK
@ActionAidUK

ActionAid is a charitable company limited by guarantee and registered in England and Wales (Company number 01295174). England and Wales charity number 274467, Scottish charity number SC045476. Registered Office 33-39 Bowling Green Lane, London EC1R 0BJ.